# በሶማሌ እና ሐረሪ ክልሎች በተካሄደዉ ምርጫ በተመዘገቡ ምልከታዎች ዙሪያ የቀረበ ቀዳሚ መግለጫ

የኢትዮጵያ ህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር

የኢትዮጵያ ህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር
ስ.ቁ: - **0115 50 87 83**
ኢሜል:- **info@ewla-et.org /ewla1995@gmail.com**
ዌብሳይት:- **WWW.ewla-et.org**
መስከረም 22 2014 ዓ.ም ፤ አዲስ አበባ

# መግቢያ

ኢትዮጵያ እንደሚታወቀዉ 6ኛዉን ሃገረራዊ እና ክልላወዊ ምርጫ ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም በስድስተት (6) ክልሎች እና ሁለት (2) ከተማ አስተዳደሮች አካሂዳለች፡፡ ነግር ግን በፀጥታ ችግሮች ፣ በምርጫ ሂደት አስተዳደር እና አሰራር ክፍተቶች ምክንያት በተወሰኑ የሃገሪቱ ክፍሎች በተለይም በሶማሌና ሐረሪ ክልሎች ምርጫ ባለመካሄዱ የምርጫ ጊዜ እንዲራዘም መደረጉ የታወሳል፡፡

በዚህ መሰረት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጿጉሜ 1 2013 ዓ.ም ምርጫ ባልተደረገባቸዉ አካባቢዎች ምርጫ እንደሚካሄድ ያሳወቀ ቢሆንም የድምፅ መስጫ ቀኑ ለሁለተኛ ጊዜ እንደተራዘመ በማሳወቅ መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም በሶማሌ እና ሐረሪ ክልሎች እንዲራዘም የተደረገዉ ምርጫ እንደሚካሄድ እንዲሁም በተወሰኑ የደቡብ ብሔርበሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል አካባቢዎች ምርጫ እና የህዝብ ዉሳኔ አሰጣጥ እንደሚደረግ ገልጿል፡፡

የኢትዮጵያ ህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም በተካሄደዉ 6ኛዉ ሃገር-ዓቀፍ ምርጫ ታዛቢዎችን በመመልመልና በማሰልጠን ባሰማራቸዉ ታዛቢዎች አማካኝነት የምርጫ ሂደቱ አካታችነትንና በተለይም የሴቶችን ሙሉ እና እኩል ተሳትፎ መቃኘት የሚያስችል ምልከታ (የመታዘብ ስራ) አከናዉኗል፡፡ ማህበሩ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ በሚፈፀሙ ጥቃቶችን በሚመለከት በሶማሌ እና ሐረሪ ክልሎች መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም በተካሄደዉ ምርጫ ምልከታ የሚያደርጉ 23 ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎችን ከአካባቢዎቹ በመመልመል አሰልጥኖ አሰማርቷል፡፡ ታዛቢዎቹ በድምፅ መስጫዉ ቀን መራጮች ወደ ድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ሲደርሱ ጀምሮ ፣ በድምፅ መስጠት ሂደቶች ፣ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎችን መዝጊያ ሂደት እና ወሳኝ ክስተቶችን በሚመለከት የሚኖራቸዉን ምልከታ መመዝገብ የሚያስችላቸዉ አራት ወጥ መጠይቆች ተዘጋጅተዋል፡፡

ይኸ የማህበሩ ቀዳሚ ሪፖርት የተዘጋጀዉ ታዛቢዎቹ በድምፅ መስጫዉ ቀን በምርጫ ጣቢያዎች ተዘዋዉረዉ ምልከታ በማድረግ ሞልተዉ ባጠናቀቋቸዉ መጠይቆች መሰረት ነዉ፡፡ ታዛቢዎቹ በምርጫ ሂደት በሴቶች ላይ የሚፈፀምን ጥቃት አስመልክቶ በነበራቸዉ የመታዘብ ሂደት 22 መራጮች ወደ ድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ሲደርሱ የተደረጉ ምልከታዎችን ፣ 59 በድምፅ መስጠት ሂደቶች ላይ የተደረጉ ምልከታዎችን እና 19 በድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የመዝጊያ ሂደቶች የተደረጉ ምልከታዎችን በማድረግ መጠይቆችን ሞልተዉ ማጠናቀቅ ችለዋል፡፡ በተጨማሪም ምልከታ ባደረጉባቸዉ የምርጫ ጣቢያዎች የተመለከቷቸዉን 4 (አራት)ወሳኝ ክስተቶች ሪፖርት አድርገዋል፡፡

# በተደረገዉ ምልከታ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች

## 1. ከድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ዉጪ ያለ ሁኔታ

የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች ምልከታ ባደረጉባቸዉ 59 የምርጫ ጣቢያዎች መካከል በ39 ጣቢያዎች መራጮች ተሰልፈዉ የተመለከቱ ሲሆን በ20 ጣቢያዎች ግን ታዛቢያዎቹ ምልከታ ለማድረግ ሲደርሱ ምንም አይነት ሰልፍ አለመታዩትን ተመልክተዋል፡፡ በተጨማሪም በ31 የምረጫ ጣቢያዎች ላይ ለመወንዶች እና ለሴቶች የተለዩ ሰልፎች እንደነበሩ የተመለከቱ ሲሆን በ8 ጣቢያዎች ላይ ግን ለሴቶች እና ወንዶች የተለየ ሰልፍ እንዳልነበረ ታዝበዋል፡፡

በኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች ምልከታ በተደረገባቸዉ 42 ድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ነፍሰ-ጡር (እርጉዝ) ሴቶች እና የሚያጠቡ እናቶች ከነበሩ ሰልፎች ቀድመዉ ድምፅ እንዲሰጡ መደረጉን የተመለከቱ ሲሆን በሁለት ጣቢያዎች ግን ቅድሚያ እንዳልተሰጣቸዉ ታዝበዋል፡፡ የማህበሩ ታዛቢዎች ምልከታ ካደረጉባቸዉ 59 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል በ30 ጣቢያዎች ዉጪ (በቅርብ ርቀት) ላይ ፀትታ አስከባሪ አካላት ወይም የጦር ሃይሎች እንደነበሩ ታዝበዋል፡፡

### 2. የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ተደራሽነት

የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች ምልከታ ካደረጉባቸዉ 59 የምርጫ ጣቢያዎች መካከል 54 ጣቢያዎች የአካል ጉዳት ላለባቸዉ ወይም እንደልብ ለመንቀሳቀስ ለሚቸገሩ (ለምሳሌ፡- አረጋዊያን ፣ ሕፃናትን ለሚይዙ) መራጮች በቀላሉ መድረስ (መግባት) የሚችሉባቸዉ እንደነበሩ ታዝበዋል፡፡ ከነዚህ መካከል አብዛሃኞቹ ለወንዶችም ሆነ ለሴቶች በቀላሉ መግባት የሚችሉባቸዉ ሆነዉ እንዳገኟችም ተመልክተወዋል፡፡

### 3. በምርጫ ሂደት ባለድርሻ አካላት መካከል የነበረዉ የስርዓተ-ፆታ ሚዛናዊነት

የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎቹን ባሰማራባቸዉ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የነበረዉ የሴቶች  የምርጫ አስፈፃሚነት (ሰራተተኝነት) ዉክልና አናሳ ነበር፡፡ የማህበሩ ታዛቢዎች ምልከታ ካደረጉባቸዉ 59 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል 37 ጣቢያዎች በወንድ ሊቀመናብርት ይመሩ እንደነበረ እና ቀሪ 22 ጣቢያዎች ላይ ሴት ሊቀመናብርት እንደተሳተፉ ተመልከተዋል፡፡ መምልከkታ ከተደረገባቸዉ ከ59 ምርጫ ጣቢያዎች መካከል በ2 ጣቢያዎች ላይ ደግሞ አንድም ሴት በምርጫ አስፈፃሚ አባልነት እንዳልተካተተ ታዝበዋል፡፡

በተመሳሳይ በምርጫ የባለድርሻ አካላት መካከል ማለትም በታዛቢነት ፣ ጋዜጠኝነት እና ተፎካካሪ ፓርቲ ተወካይነት የነበረዉ የሴቶች ተሳትፎ አናሳ እንደነበር ተመልከተዋል፡፡ የማህበሩ ታዛቢዎች ምልከታ ከካደረጉባባዉ 59 ጣቢያዎች መካከል 11 የድምፅ መስጨጫ ጣቢያዎች ላይ ሴት ታዛቢዎች ፣ ጋዜጠኘኞች እና የተፎካካሪ ፓርቲ ተወካዮች  እንዳልነበሩ የተመለከቱ ሲሆን በ41 ድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ሴት ታዛቢዎች መመልከታቸዉን ፤ በ6 ድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ደግሞ የተወሰኑ ሴት ታዛቢዎች ፣ ጋዜጠኞችና የተፎካካሪ ፓርቲ ተወካዮችን እንዲሁም በ4 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የተወሰኑ የተፎካካሪ ፓርቲ ተወካዮችን መመልከታቸዉን ታዝበዋል፡፡

### 4. የምርጫ ሂደት ዝግጁነት እና ለኮቪድ-19 መከላከል ድንጋጌዎች የነበረ መጣጣም

በኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች የተጎበኙት 59 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ላይ አስፈላጊ የሚባሉ የምርጫ ቁሳቁሶችን ያሟሉ እንደነበሩ ተመልከተዋል፡፡

ከ59 የምርጫ ጣቢያዎች መካከል በ51 ጣቢያዎች ሲሰሩ የነበሩ ሁሉም የምርጫ አስፈፃሚ ሃላፊዎችና በ3 ጣቢያዎች የሚሰሩ የተወሰኑ ሰራተኞች የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል (ማስክ) መልበሳቸዉን የተመለከቱ ሲሆን በ5 የምርጫ ጣቢያዎች ግን የምርጫ አስፈፃሚ ሃላፊዎች የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል (ማስክ) እንዳልለበሱ ታዝበዋል፡፡

### 5. ሴት መራጮች የመምረጥ መብታቸውን ያጡባቸው ክስተቶች

ከ59 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ዉስጥ በ3ቱ ከ1-10 የሚሆኑ ሴት መራጮች በተለያየ ምክንያት እንዲመርጡ አልተፈቀደላቸውም ነበር፡፡ ይኽም ለመምረጥ ብቁ ሆነዉ ባይገኙም በምርጫ ለመሳሳፍ ያለዉን ፍላጎት ያመላክታል፡፡ የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች ምልከታ ካደረጉባቸዉ 59 የምርጫ ጣቢያዎች መካከል በ10 ጣቢያዎች ከ1-10 የሚሆኑ ሴት መራጮች ምንም አይነት እገዛ የማያስፈልጋቸው ቢመስሉም ድምፅ ሲሰጡ እገዛ ተደርጎላቸዋል፡፡ በ7 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የሚሰሩ የምርጫ ጣቢያ ሰራተኞች እነዚህን እገዛዎች ለማስቆም ጣልቃ እንዳልገቡም ተመልክቷል፡፡

## 6. ወሲባዊ ትንኮሳ እና በምርጫ ሂደት በሴት መራጮች ላይ የተፈጸመ ጥቃት

በአጠቃላይ የማህበሩ ታዛቢዎች ምለከታ ባደረጉባቸዉ 59 የድምፅ መሰስጫ ጣቢያዎች ዉስጥ እና ዉጪ ምንም አይነት ፆታዊ ትንኮሳ (የቃላት ወይም አካላዊ) እንዲሁም በሴቶች ላይ የተፈፀመ ጥቃት ወይም የሃይል ተግባር አልተመዘገበም፡፡

## 7. ምርጫን ማጠናቀቅ እና ድምፅ ቆጠራ

በሐረሪ ክልል ከነበረዉ የመራጮች ረጃጅም ሰልፎች የተነሳ የኢትዮጲያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ባስተላለፈዉ ዉሳኔ መሰረት በክልሉ የነበረዉን የምርጫ ማጠናቀቂያ ግዜ ከምሽቱ 12 ሰዓት መሆኑ ቀርቶ እስከ ምሽቱ 2 ሰዓት ድረስ ማለትም ለ2 ሰዓታት እንዲራዘም ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ከ23 የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች መካከል የድምፅ መስጠት ሂደቱ እና ድምፅ ቆጠራዉ እስኪጠናቀቅ መቆየት ያልቻሉት 4 ታዛቢዎች ብቻ ነበሩ፡፡

የማህበሩ ታዛቢዎች ምልከታ ባደረጉባቸዉ 21 የምርጫ ጣቢያዎች የነበረዉ የምርጫ ማጠናቀቂያን እና ድምፅ ቆጠራ ሂደት በሁከት ወይም በሌሎች ክስተቶች መስተጓጎል እንዳልደረሰ ታዝበዋል፡፡

የማህበሩ ታዛቢዎች የምርጫ ማጠናቀቂያን እና ድምፅ ቆጠራን በሚመለከት ምለከታ ባደረጉባቸዉ 19 የድምፅ መሰስጫ ጣቢያዎች ላይ ምንም አይነት በሴቶች ላይ የተፈፀመ ጥቃት ወይም የሃይል ተግባር አልተመዘገበም፡፡

## 8. የማህበሩ ታዛቢዎች ምርጫውን ለመታዘብ ያላቸው ሙብቶች

የኢትዮጵያ ህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ያሰማራቸዉ ሁሉም (23ቱም) ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎች ወደ ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ለመግባትም ሆነ በድምፅ አሰጣጥ እና በመዝጊያ ሂደቶች በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች ወይም የሃይል ተግባሮችን በሚመለከት ምልከታ ለማድረግ ያጋጠማቸዉ ተግዳሮት አልነበረም፡፡

## 9. ወሳኝ ክስተቶች

4 ወሳኝ ክስተቶች በኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች ተመዝግበዋል፡፡ ከ4ቱ ወሳኝ ክስተቶች መካከል 1ኛዉ የተመዘገበዉ በአንድ የምርጫ ጣቢያ የምርጫ ኮሮጆ በሚከፈትበት ወቅት ያልታሸገ ኮሮጆ በመሆኑ በኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ አማካኝነት ታዛቢዎች ፣ የምርጫ ቦርድ ሃላፊዎች እና የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች በተገኙበት ኮሮጀዉ ዉስጥ ያሉ ዶክመንቶች እንዲቆጠሩ በማድረግ በደቂቃ ዉስጥ መፍትሄ እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡ ሆኖም በማህበሩ ታዛቢ የወሳኝ ክስተቶች ቅፅ እንዲሞላ አድርገናል፡፡

2 የወሳኝ ክስተት ቅፆች ደግሞ በድምፅ መስጫ ጣቢያ ዘግይቶ መዘጋት ዙሪያ የተመዘገበቡ ነዉ፡፡ የማህበሩ ታዛቢዎች በምርጫ ጣቢያዎቹ በማምሽት የድምፅ መስጫ ጣቢያዎቹ እስከሚዘጉ ለመቆየት ደህንነት ስላልተሰማቸዉ የመዝጊያ ሂደቱን መታዘብ ሳሳችሉ ቀርተዋል፡፡ ከ4ቱ ወሳኝ ክስተቶች የመጨረሻዉ ደግሞ  በድምፅ መስጫ ኮሮጆዉ አቅራቢያ ባልተፈቀደለት ግለሰብ አማካኝነት ለመራጮች ያልተገባ እገዛ የማድረግ ጥያቄ ሲቀርብ እንደነበር ተመዝግቧል፡፡

## ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ታዛቢዎች በሶማሌ እና ሐረሪ ክልሎች በተካሄደዉ ምርጫ በሴቶች ላይ የሚፈፀምን ጥቃት ወይም የሃይል ተግባር አስመልክቶ ያለማንም ጣልቃገብነት ምልከታ ማድረግ ችለዋል፡፡ የማህበሩ ታዛቢዎች ምልከታ ባደረጉባቸዉ 78 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በሁሉም ለድምፅ አሰጣጥም ሆነ ለመዝጊያ እና ድምፅ ቆጠራ የሚያስፈልጉ ሂደቶችን ለመከወን የሚያስችል ዝግጅት የነበራቸዉ አስፈላጊ የምርጫ ቁሳቁሶችም የተሟሉ ነበሩ፡፡ የማህበሩ ታዛቢዎች በሴቶች ላይ የሚፈፀምን ጥቃት ወይም የሃይል ተግባር አስመልክቶ ምከታ ባደረጉባቸዉ በአብዘሃኛዉ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች (54) በድምፅ መስጠት ሂደት ወቅት ሁሉም በሚባል ደረጃ የምርጫ ጣቢያ ሰራተኞች የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስኮችን በመልበስ የኮቪድ 19 መከላከያ ደንብን አክብረዋል፡፡

በምርጫ የባለድርሻ አካላት መካከል የሴቶች ዉክልና አናሳ ነበር፡፡ የማህበሩ ታዛቢዎች ምልከታ ካደረጉባቸዉ 59 የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል 37 ጣቢያዎች በወንድ ሊቀመናብርት ይመሩ እንደነበረ እና ቀሪ 22 ጣቢያዎች ላይ ሴት ሊቀመናብርት እንደተሳተፉ ተመልክተዋል፡፡ በ11 የድምፅ መስጨጫ ጣቢያዎች ደግሞ ሴት ታዛቢዎች ፣ ጋዜጠኞኞች እና የተፎካካሪ ፓርቲ ተወካዮች አልተሳተፉም፡፡

የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች ምልከታ ካደረጉባቸዉ 59 የምርጫ ጣቢያዎች መካከል በ3 የምርጫ ጣቢያዎች ከ1-10 የሚሆኑት ሴት መራጮች በመራጮች ዝርዝር ውስጥ ባለመገኘታቸው ድምፅ መስጠት ያልቻሉ ሲሆን በአንድ የምርጫ ጣቢያ ከ1-10 የሚሆኑ ሴት መራጮች በተለያየ ምክንያት መምረጥ ሳይችሉ ቀርተዋል፡፡ የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች ምልከታ ካደረጉባቸዉ 59 የምርጫ ጣቢያዎች መካከል በ10 ጣቢያዎች ከ1-10 የሚሆኑ ሴት መራጮች ምንም አይነት እገዛ የማያስፈልጋቸው ቢመስሉም ድምፅ ሲሰጡ እገዛ ተደርጎላቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር (ኢ.ሕ.ባ.ሴ.ማ) ከሁለቱም ክልሎች የተቀበላቸዉን የታዛቢዎቹን ምልከታዎች ሰኔ 14 2013 ዓ.ም ከተካሔደዉ ምርጫ ግኝቶች ጋር በማዋሃድ የማጠቃለያ የምርጫ ምልከታ ሪፖርቱን በመጪዎቹ ሳምንታት ለህዝብ የሚያቀርብ ይሆናል፡፡

## ስለ እኛ

የኢትዮጵያ ሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር በፌደራል ደረጃ በ1987 ዓ.ም የተቋቋመ ፤ በበጎ አድራጎት ማህበራትና ድርጅቶች ኤጀንሲ የተመዘገበ የሲቪክ ማህበር ሲሆን ላለፉት ከ25 ዓመታት በላይ የሴቶችን ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ሕጋዊ መብቶች እንዲታወቁ በማድረግ ሴቶች በሕገ-መንግስቱ እና በሌሎች ሕጎች በተመላከቱ መብቶቻቸዉ እንዲጠቀሙ የሚያግዙ ስራዎችን ሲሰራ ቆይቷል ፡፡

የማህበሩ ግብ ሴቶች በሁለንተናዊ ዘርፍ እኩል ተጠቃሚና ተሳታፊ እንዲሆኑ አስተዋፅኦ ማድረግ ሲሆን በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ፆታዊ ጥቃቶችን መከላከልና ለሴቶች ከጥቃት የፀዳ ከባቢን መፍጠርን አላማዉ አድርጎ የተለያዩ ስልቶችን በመንደፍ በዋና ፅ/ቤቱ አዲስ አበባ እና በ8 የክልል ከተሞች ማለትም በአዳማ ፣ በሐዋሳ ፣ በባህር ዳር ፣ በድሬ ዳዋ ፣ በጋምቤላ ፣ በአሶሳ ፣ በጅግጅጋ እና ሰመራ በሚገኙት ቅርንጫፍ ጽ/ ቤቶቹ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

የማህበሩ አገልግሎት ለሁሉም ተደራሽ እንዲሆን ከማድረግ አንፃር ማህበሩ ባሉት የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ስር በሚገኙ ዞን እና ወረዳዎች ላይ ከማህበረሰቡ በተዉጣጡ በጎ ፈቃደኞች አማካኝነት የሚሰጠዉ አገልግሎት እንዲቀጥል እየሰራ ሲሆን እስከአሁን ድረስም በሃገሪቱ በአጠቃላይ 54 በጎ ፈቃደኛ ኮሚቴ ማዕከሎችን አቋቁሟል፡፡

ከነዚህ አማራጮች በተጨማሪ በተለይ ማህበሩ በጉልህ የሚታወቅበትን ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት በመላ ሃገሪቱ ለሚገኙና ድጋፍ ለሚሹ ሴቶች ለማዳረስ ይረዳ ዘንድ ነፃ የስልክ ጥሪ ማዕከል/Hotline servise በማቋቋም በ7711 አጭር የነፃ ስልክ መስመር አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

## ስለ “በምርጫ ሂደቶች ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች” ፕሮጀክት

የኢትዮጵያ ሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ከናሽናል ዲሞክራቲክ ኢንስቲቲዉት (ኤን.ዲ.አይ) ጋር ባደረጉት የአጋርነት ስምምነት እና ከዩናይትድስቴት ኤጀንሲ ፎር ኢንተርናሽናል ዲቨሎፐመንት (ዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ) በተገኘ የገንዘብ እና የቴክኒክ ድጋፍ ስር “በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች” በሚል ፕሮጀክት ነድፎ እየሰራ ይገኛል፡፡ የፕሮጀክቱ ዋና አላማ በቅድመ-ምርጫ ወቅት እና በምርጫ ቀን ምልከታዎችን (የመታዘብ ስራዎችን) ለማድረግ እንዲሁም በነፃ የስልክ ጥሪ መስመር 7711 ከማህበረሰቡ ጥቆማዎች ለመቀበል ነዉ፡፡ የምልከታ ግኝቶችን እና በነፃ ጥሪ ማዕከሉ የሚመዘገቡ ግኝቶች ማህበሩ ወደፊት በዘርፉ ለሚያደርጋቸዉ የግፊት (የሙግታ) ስራዎች ግብዓት የሚሆኑ ይሆናል፡፡